የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

# የሥርዓተ-ፆታ ፖሊሲ ውይይት
# Gender Policy Dialogue

የሥርዓተ-ፆታ ፖሊሲ ውይይት ተከታታይ እትም ቁጥር 2

Gender Policy Dialogue Series No. 1



# ሥርዓተ-ፆታ እና ድህነት

አዘጋጅ፦ ዘነበወርቅ ታደሰ

አዲስ አበባ

ግንቦት 1995

# ማውጫ

**መግቢያ**........................................................................................................................ i
*ዘነበወርቅ ታደሰ*

**በሥርዓተ-ፆታና በድህነት ዙሪያ የተደረገ ውይይት**.......................................................... 1
*ተመስገን አበጀ*
*ፀዳለ ልባሱ*
*ኤልሳቤጥ ስ*

**ድህነትና ሥርዓተ-ፆታ**................................................................................................ 7
*ጥሩወርቅ ዳንዶ*

© 2003 Forum for Social Studies and the Authors.

**የሽፋን ፎቶ፡-** ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ክምችት
ድህነትና የሴቶችን ህይወት የሚያንፀባርቅ

**ዝግጅት፡-** እሸቱ በቀለ

**ትየባና ለህትመት ዝግጅት፡-** ምህረት ደምሰው

*በዚህ ህትመት ውስጥ የቀረቡት ሀሳቦች የፅሁፍ አቅራቢዎቹን እንጂ የማኅበራዊ ጥናት መድረክን ወይም የአማካሪ ቦርዱን አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ የማያንፀባርቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡*

# <u>መግቢያ</u>

*የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በዚህ ዓመት በየሁለት ወሩ የሚካሄድና ከዓመት በላይ የሚቆይ የውይይት መድረክ ፕሮግራም ጀምሯል። ከነዚህም አንደኛው የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ውይይት ሲሆን (ማለትም የዛሬው ፕሮግራም ሲሆን)፣ ሁለተኛው የብዙኃን ድርጅቶችና የአካባቢ ፖሊሲ ውይይት መድረክ ነው። በዛሬው ዕለት የሚካሄደው የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ውይይት መድረክ ሁለተኛውና "ሥርዓተ-ጾታ እና ድህነት" ላይ ያተ ረ ውይይት ይሆናል።*

*የዛሬ ሁለት ወር በተካሄደው ውይይት ላይ ላልተገኛችሁ ተሳታፊዎች የዚህን የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ውይይት መድረክ ፕሮግራም ዋና ዋና ዓላማዎች ጠቅሼ ላልፍ እወዳለሁ።*

*የዚህ የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ዋነኛውና መሰረታዊ ዓላማ የተለያዩ አካላትን የድጋፍ ሃሳብ ለማሰባሰብ፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ እንዲሁም ለወደፊቱ ለብዙሃን ድርጅቶችና ሌሎች ህዝባዊ ውይይቶች የሚሆኑ የተለያዩ ሥርዓተ-ጾታ ነክ ጉዳዮችን መለየት የሚያስችል አጠቃላይ የሆነ የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ሰነድ ለመንደፍ ነው።*

*ይህም ዓላማ ሊሳካ የሚችለው እያንዳንዱ የውይይቱ ተሳታፊ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ ኢትዮጵያ ላይ ያተ ረ እናንተም ሆናችሁ ድርጅታችሁ ወይንም የምታወቁት ሰው ያዘጋጁትና ከዚህ ዓላማ ጋር ተያያዥ የሆነ ጥናታዊ ስራ ካለ ብትጠቁሙን ለፕሮግራሙ ስኬታማነት በጣም የሚረዳን መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ።*

*በተላከላችሁ የጥሪ ወረቀት ላይ እንደተገለጸው የዛሬው የውይይት መድረክ የሚያተኩረው "ሥርዓተ-ጾታ እና ድህነት" ላይ ነው። ይህንን መድረክ ከሌላው ለየት የሚያደርገው፣ በተመራማሪዎች ጥናት ላይ ብቻ ያተ ረ ሳይሆን ከድሀው ህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ተሳታፊዎች ስለ ሥርዓተ-ጾታ እና ድህነት ከህይወት ልምዳቸው አንጻር ያላቸውን አስተሳሰቦች እንደዚሁም ከድህነት ለመላቀቅ ያደረጓቸውን ጥረቶች ስለሚገልጹልን ነው። በተጨማሪም በጥናት ላይ የተመሰረተ አስተያየትም እናዳምጣለን። እነዚህ የውይይት መነሻ አቅራቢዎች የሚያበረክቱልን ሀሳብ መንደርደሪያ ሲሆን የውይይቱ ዋና አካል ከእናንተ ከተሳታፊዎች የሚመነጩ ጥያቄዎችና ተጨማሪ አስተያየቶች ስለሆኑ በዚህ አጋጣሚ በንቃት እንድትሳተፉ እጋብዛለሁ። ይህ ውይይት ሰፋ ላለ ህዝብ እንዲዳረስ በልዩ ልዩ ህትመቶችና እንደዚሁም በማህበራዊ ጥናት መድረክ በኤፍ.ኤም የ"ደወል ሬዲዮ" ፕሮግራም ይተላለፋል።*

*እንደሚታወሰው ሁሉ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ መንግስት ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ በሚያዘጋጅበት ወቅት ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲህ አይነት ሀገር-አቀፍ ሰነድ በመንግስት ብቻ መቀረጽ ስለሌለበት ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተዋጽኦ ሊ ረው ይገባል በሚል የተለያዩ መድረ ች በማዘጋጀት ድምጻቸውን ለማሰማት ሞክረዋል። በዚህም ሂደት ውስጥ የማህበራዊ ጥናት መድረክ ግንባር-ቀደም ሚና ተጫውቷል። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ሲታይ መንግስት የነደፈው ስትራቴጂም ሆነ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ባደረገው ውይይት ላይ ስለ ድህነትና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር።*

*በዛ ተሞክሮ ላይ በመመስረት፣ ይህ በዚህ ዓመት የተጀመረው የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ ውይይት በዛሬው ውይይት ሳይወሰን በሥርዓተ-ጾታ እና በድህነት መካከል ያለውን ዘርፈ-ብዙ ግንኙነቶች በጥልቀት የሚተነትንና ያለውን የሥርዓተ-ጾታ ልዩነት ለማስተናገድ የተዘጋጁ በርካታ ዘርፍ ያሉት አቀራረብ ላይ የተመሰረተ እና ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የድህነት ቅነሳ መርሀ-ግብር የሚጠቁም እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።*

**ዘነበወርቅ ታደሰ**
*አስተባባሪ*

# በሥርዓተ-ፆታና በድህነት ዙሪያ የተደረገ ውይይት፣

## ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም

አቶ ተመስገን አበጀ ፕሮፕራይድ በተባለው አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ተጠቃሚ እና በወረዳ አምስት ውስጥ በድርጅቱ በተቋቋመው የልማት ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው:: አቶ ተመስገን በመግለጫቸው እንዳሳዩት የእሳቸው ወረዳ የሚያቅፈው በአዲስ አበባ ውስጥ የድሆች ድሃ የሆነውን የሕብረተሰብ ክፍልና ከዚህም ውስጥ ድሃ ሴቶች ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ነው:: ስለድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የሰሙ መሆኑን ገልጸው ነገር ግን መንግስት ድጋፍ ሲሰጥ ያላዩ መሆኑንና ድህነት የመቀነስ ተነሳሽነት ካለ ተግባራዊነቱ መጀመር ያለበት ከእርሳቸው ወረዳ መሆን እንደሚገባው ተናግረዋል:: እንደእርሳቸውም በአካባቢያቸው ድህነትን ለመቀነስ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ቢኖር ፕሮፕራይድ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል::

አቶ ተመስገን ከድህነት ጋር የተያያዙ ብለው ካቀረቧቸው ችግሮች ውስጥ ስራ አጥነት አንዱ ነው:: በወረዳቸው ውስጥ ያሉት ወንዶች ጥንካሬውና የመስራት ጊዜው ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ነገር ግን የስራ ዕድል በማጣታቸው ምክንያት ጊዜያቸውን በከንቱ እንደሚያቃጥሉ አውስተዋል:: በተጨማሪም በማህበረሰባቸው ውስጥ ሌላኛው ችግር የትምህርት ዕድል ማጣት መሆኑን ገልፀዋል:: ፕሮፕራይድ በወረዳው ያሉትን የተወሰኑ ህፃናት በወረዳው በሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ባያደርግ ሁኔታው ከዚህ የከፋ ይሆን ነበር ብለዋል::

መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን ለመቀነስ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያሳዩት ጥረት ምን መሆን እንዳለበት ሲጠቅሱ ሁለቱም ወገኖች በእውነተኛ መንፈስ በመተባበር በሚያደርጓቸው ጥረቶች በከፍተኛ ደረጃ ህብረተሰቡን ሁሉ ተካፋይ ማድረግና ገንቢ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ተግባራዊ መንገዶችን እንዲቀይሱ አሳስበዋል::

አቶ ተመስገን የፕሮፕራይድን ጥረቶች አፅንኦት ሰጥተውታል:: ድርጅቱ ለማህበረሰቡ አባላት የአነስተኛ ንግድ ስልጠና በመስጠት ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል:: እንደሳቸው አባባል ከ70 በላይ ድሃ ግለሰቦች የስልጠናው ተጠቃሚ ሆነዋል:: በተጨማሪም ድርጅቱ የብድር አገልግሎት እንደሚሰጥ ጠቅሰው በዚሁ ጥረትም በወረዳቸው ውስጥ የሚገኘው ነዋሪ የራሱንና የቤተሰቡን የእለት ጉርስ እንዲያገኝና የተሻለ ህይወት እንዲመራ ረድቷል ብለዋል:: በተጨማሪም ድርጅቱ የህክምና እንክብካቤ አገልግሎት ለማህበረሰቡ አረጋዊያን መስጠቱን ገልፀዋል:: እሳቸው እስከሚያውቁት ድረስ በዚህ ጥረት 9 የሚሆኑ አረጋውያን ተጠቃሚ ሆነዋል::

ሁለተኛዋ ተናጋሪ ወ/ሮ ፀዳለ ልባሱ የተባለች ወጣት የእንጦጦ ወረዳ አካባቢ ነዋሪና የፕሮፕራይድ ተጠቃሚ ነች:: ከድርጅቱ ባገኘችው እርዳታ በአካባቢዋ የኤች አይ ቪ ኤድስ ክበብ አባልም ነች:: መግለጫዋ ያተኮረው በሥርዓተ ጾታና በድህነት መካከል ስላለው ግንኙነትና ልዩነት ላይ ነበር:: ሴቶች የመጀመሪያው የድህነት ገፈት ቀማሽ መሆናቸውን ጠቅሳ ስለ ድህነት ማስወገድ በምንነጋገርበት ወቅት ሴቶች ወደ ጐን ሊተው እንደማይችሉ አስምራበታለች:: አክላም በቤት ውስጥ ሥራ ሴቶች ከፍተኛውን ኋላፊነት የሚሸከሙና የቤተሰባቸው ሕልውና እንዲቀጥል ቀን ከሌሊት የሚጥሩ መሆናቸውን ገልጻ ይህ ሆኖ ሳለ ግን የትምህርት እድል እና የመሳሰሉት ጥቅሞች ሲነሱ ለሴቶች የሚሰጠው እድል እጅግ አናሳ ነው ብላለች::

አቅራቢዋ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን የሥራ ክፍፍል ለማሳየትም የራሷን የሕይወት ልምድ አካፍላለች:: ወ/ሮ ፀዳለ የአንድን ቤተሰብ ገቢ ለማስገኘት

በዋናነት ኋላፊነቱ በሴቶች ላይ እንደሚወድቅ ጠቅሳ በእርሷ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች እንጀራ ጋግረው በመሸጥ ቤተሰባቸውን እንደሚመግቡም ተናግራለች። በኘሮኘራይድ በተዘጋጀው የሥርዓተ-ጾታ ስልጠና ላይ ተሳታፊ ለመሆን ወ/ሮ ፀዳለ ቤተሰቦቿ የፈቀዱላት እንጀራ መሸጧንና ቤተሰቧን መመገብ መቀጠሏን ስለቻለች ብቻ እንደሆነም ጨምራ ጠቅሳለች።

ወ/ሮ ፀዳለ በተጨማሪም ስልጠናውን በመካፈሏ ያገኘችውን ጥቅም ጠቅሳለች። ስልጠናው ራሷንና ቤተሰቧን በመለወጥ ረገድ የሥርዓተ-ጾታንና የሥነ-ተዋልዶ ግንዛቤያቸውን እንዳሰፋ ገልጻለች። በአሁኑ ወቅት በቤቷ አካባቢ ጥቂት ገንቢ ለውጦች መኖራቸውን ጠቅሳለች። የቤተሰቧ አባሎች በሥርዓተ ጾታ ላይ የተዘጋጁ የስልጠና ጽሁፎችን ካነበቡ በኋላ አመለካከታቸው እንደተቀየረ ገልጻለች። አባቷ ቀደም ሲል በጠዋት የሚነሱ፣ ፊታቸውን ታጥበው፣ ቁርስ በልተው ይወጡ የነበሩት አሁን በመቀየር ቢያንስ ከቤት ከመውጣታቸው በፊት አልጋቸውን አንጥፈው መውጣት መጀመራቸውን ገልጻለች።

አቅራቢዋ በመቀጠል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጉዳይንም አንስታለች። በአካባቢዋ በአነስተኛ የኤድስ ክበብ መሳተፏ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለወረርሽኙ በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጡ መሆኑን ለመገንዘብ እንዳስቻላት አሳውቃለች። አክላም ሴቶች በባሕል ተጽእኖ ምክንያት ስለ ሥነተዋልዶ ጤና እውቀት የማግኘት እድል እንደተነፈጋቸውና በዚህም ምክንያት ለገዳዩ የኤች አይቪ ቫይረስ መጋለጣቸውን ጠቅሳለች።

ወ/ሮ ፀዳለ በአካባቢያዋ ብዙ ሴቶች በሀይል እንደሚደፈሩና ይህም በቫይረሱ የመጠቃት እድላቸውን ከፍ እንደሚያደርገው ገልጻለች። ይሁን እንጂ ጥፋተኞቹ ተገቢው ቅጣት ስለማይወሰድባቸው ወንጀሉን በተደጋጋሚ ይፈጽማሉ ብላለች። የሚመለከታቸው አካላት በነዚህ ወንጀለኞች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ እንዲወስዱም ጥሪ አቅርባለች። በመጨረሻም የተሻለ ግንዛቤ ላስጨበጣት ኘሮኘራይድ ያላትን ከልብ የመነጨ ምስጋና አቅርባለች።

ሦስተኛዋ ተናጋሪ የአኮርድ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ የሆነችው ወ/ት ኤልሳቤጥ ስዩም የተባለች ወጣት ስትሆን የመጣችውም ከአቃቂ በሰቃ ነው። ድህነትን አስመልክቶም አጭር ማብራሪያ ሰጥታለች። ወ/ት ኤልሳቤጥ ንግግሯን የጀመረችው ድህነትን በተመለከተ የግል ልምዷን በመንተራስ ነበር። በጣም ደሀ ከሆነ ቤተሰብ የመጣች መሆኑን ገልጻ ቤተሰቧን ለመርዳት በልጅነቷ ትምህርቷን ለማቋረጥ እንደተገደደች ጠቅሳለች። በአኮርድ ኢትዮጵያ አማካኝነት የብድር አገልግሎት በማግኘቷ አነስተኛ ንግድ መጀመሯን ገልጻለች።

ወ/ት ኤልሳቤጥ በመቀጠል ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መርዳት የሚችሉበት መንገድ የሌላቸውና በትንሽ እርዳታ የተሻለ ሕይወት መምራት የሚችሉ ከእሷ በባሰ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሰዎች እንዳሉ ጠቅሳለች። በመጨረሻም ድህነት ቅነሳን አስመልክቶ በአኮርድ ኢትዮጵያ ከሚደረገው ጥረት በቀር በአካባቢዋ በመንግስት ምንም አይነት ጥረት ሲደረግ አለማየቷን ገልጻለች።

## ጥያቄዎችና አስተያየቶች

የአቅራቢዎቹ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ የስብሰባው ተሳታፊዎች በስብሰባው ጭብጦች ላይ በመመስረት አስተያየቶቻቸውንና ጥያቄዎቻቸውን አቅርበዋል። አቅራቢዎቹ በዛ ያሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር። የመጀመሪያው ጥያቄ የቀረበው ለአቶ ተመስገን ነበር። ጥያቄውም በብድር አገልግሎት በኩል ከድርጅቱ የተበደሩትን ገንዘብ መክፈል የሚያቅታቸው ሰዎች ቢኖሩ ፕሮፕራይድ ምን እርምጃ ይወስዳል

የሚል ሲሆን መልሳቸውም ፕሮፐራይድ ገንዘቡን ከመስጠቱ አስቀድሞ ስለ አነስተኛ ንግድ ስልጠናዎች ስለሚሰጥ ተበዳሪዎች ንግዳቸውን ለመምራት የሚያስችል በቂ እውቀት በማስጨበጥ አትራፊ እንዲሆኑ ስለሚያስችል የመክሰር አጋጣሚ /አደጋን/ ያስወግዳል ብለዋል። ሆኖም ግን ተበዳሪዎቹ ገንዘብ መክፍል ቢያቅታቸው ድርጅቱ ምን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል ድርጅቱ ቢጠየቅ እንደሚሻል ገልጸዋል።

ወ/ሮ ፀዳለም ፕሮፐራይድ ስለሚሰጠው ስልጠና ያላትን ሐሳብ አካፍላለች። በአካባቢያዋ ከሚገኙት 13 ቀበሌዎች ዘጠኙ በድርጅቱ እቅዶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጻ እሷን ጨምሮ በዛ ያሉ ሰዎች አነስተኛ የንግድ ድርጅትን እንዴት መምራትና አትራፊ መሆን እንደሚችሉ ሥልጠና ማግኘታቸውን ጠቅሳለች። አብዛኞቹ ተበዳሪዎችም ራሳቸውን ለመቻል የሚያደርጉት ጥረት ውጤታማ መሆኑን ጠቅሳ የተበደሩትን ብድርም መክፈላቸውንና የተሻለ ሕይወት በመምራት ላይ መሆናቸውን ገልጻለች።

አቶ ተመስገን ቀጥሎ የቀረበላቸው ጥያቄ በልማት ኮሚቴ ውስጥ ያሉት ባልደረቦቻቸው እና እሳቸው በአካባቢያቸው የሚገኙ ባለሀብቶች ድህነትን ለመቀነስ የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉ ጠይቀው እንደ ነበር የሚጠይቅ ነው። በመልሳቸውም እነዚህን ሰዎች ለማነጋገር ሙከራዎች እንዳደረጉ ነገር ግን ተጨባጭ እርዳታ እንዳላገኙ አሳውቀዋል። በተጨማሪም እሳቸውና ባልደረቦቻቸው እነዚህን ሰዎች ወደፊትም ማነጋገራቸውን እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል። አቶ ተመስገን በወረዳቸው ውስጥ ስላለው የድህነት ደረጃ እንዲያብራሩ፣ በየቤቱ ምን ያህል ሰዎች እንደሚኖሩ ፣ በወረዳቸው ውስጥ ያሉት ሰዎች በቀን ምን ያህል ጊዜ እንደሚመገቡና ስንቶቻቸው በረሃብ ምክንያት በሳምንት ወይም በወር እንደሚሞቱ ፍንጭ እንዲሰጡ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። እሳቸውም ለተሳታፊዎቹ እንዳብራሩት በቀበሌያቸው ውስጥ 324 የሚሆኑ አረጋዊያን እንደሚገኙና አብዛኛዎቹ በምግብ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ የተጠቁ መሆናቸውና በዚሁ ሳምንትም ጐረቤታቸው የሆኑ አንድ አረጋዊ በረሃብ ምክንያት መሞታቸውን ገልፀዋል።

ወ/ሮ ኤልሳቤጥም በዚሁ ጉዳይ ላይ ያላትን ልምድ በተጨማሪነት ስታቀርብ ድህነት በአካባቢያዋ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚንፀባረቅ እና በቀን ምንም የማይመገቡ ሰዎች መኖራቸውን ገልጻለች። ለዚህም በማስረጃነት በጐረቤቷ የሚገኝ አንድ ህጻን ቤተሰቦቹ ውጪ እያጠጡ ያሳደጉት እንዳለም ገልጻለች።

በእያንዳንዱ ቤት ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን ቁጥር አስመልክቶ አቶ ተመስገን ሲመልሱ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦች ቁጥር ዝቅተኛው 5 ከፍተኛው ደግሞ ከ13-15 እንደሚደርስ ገልጸዋል። በአንዳንዶቹ መኖሪያ ቤቶች በቦታ እጥረት ምክንያት ሕጻናት አልጋ ሥር እንደሚተኙ ጠቅሰዋል።

ሌላ ተሳታፊ ንግግራቸውን የጀመሩት ይህንን የውይይት መድረክ ላዘጋጀው አካል ምስጋናቸውን በማስቀደም ነው። በመቀጠልም እንዲህ አይነት የውይይት መድረኮች በክልሎችም መዘጋጀት እንዳለባቸው ገልጸው ይህም የሚያስፈልገው ውይይቱ ሀገር አቀፍ ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው ብለዋል። ተሳታፊው በሥነ-ሕዝብ ሙያ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ጠቅሰው የሴቶችን ሕይወት በቀጥታ በሚመለከቱ ጉዳዮች ሳይቀር በተለያዩ መድረኮች የሴቶች ተሳትፎ በጣም ውስን መሆኑን ጠቅሰዋል። አያይዘውም እንደገለጹት እስከ ዛሬ ድረስ ከተከታተሏቸው መድረኮች ይኽ መድረክ ሴቶች በብዛት የተሳተፉበት መሆኑንና መድረኩ በርካታ ሴቶች ተሳትፏቸው እየጨመረ መምጣቱን እንዳሳያቸው ጠቁመዋል። እኝህ ተሳታፊ ድርጅታቸው ነጻ የትምህርት እድል ሲሰጥ እና ሴቶች 40% የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ሲሰጥ አመልካቾች ወንዶች መሆናቸውንና በጣም ጥቂት ሴቶች ብቻ

እንደሚያመለክቱ ገልጸዋል። በማስከተልም ሴቶች እያሉ ለምን የእንደዚህ መሰል እድሎች ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻሉ እንዲብራራላቸው ጠይቀዋል።

ለዚህ ጥያቄ ወ/ሮ ፀዳለ በሰጠችው ምላሽ የትምህርት እጦት ከባሕላዊ ተጽእኖ ጋር ተደምሮ ሴቶች በሕዝባዊ መድረኮች ድምጻቸውን እንዳያሰሙ እንዳገዳቸው ገልጻለች። አያይዛም ከራሷ ልምድ በመነሳት ብዛት ባለው ተሳታፊ ፊት ንግግር ስታደርግ ይኸ የመጀመሪያዋ እንደሆነም ጠቅሳለች። በመጀመሪያ ወደ መድረኩ ስትቀርብ የመደንገጥ ስሜት እንዳደረባትና ቀስ በቀስ ግን ፍርሀቱ እንደለቀቃት ገልጻለች። ተመሳሳይ የፍርሀት ስሜቶች በሌሎች ሴቶች ላይ ሊከሰት እንደሚችል ጠቅሳ ለምሳሌ ያህል እህቷ በዚህ አይነት ስብስብ መሀል እንድትናገር ብትጠየቅ በፍርሃት ምክንያት ፈቃደኛ ላትሆን ወይም ለማለት ያሰበችውን በትክክል ለመናገር እንደማትችል ጠቅሳለች። በመጨረሻም ፕሮፕራይድ በዚህ መሠል ስብስብ ፊት ቆማ ለመናገር ስላስቻላት ከልብ የሆነ ምስጋና አቅርባለች።

በተመሳሳይም ስብሰባዎች ላይ ብዙ ሴቶችን ተሳታፊ ለማድረግና አመለካከታቸውን ለመለወጥ ለሴቶች ስልጠና የመስጠት አስፈላጊነትን ሃሳብ አቅርባለች። በአደባባይ የሚናገሩ ሴቶች ማግኘት ከባድ ሊሆን የቻለው በባህላዊ ተጽእኖና በትምህርት እጦት መሆኑን ጠቁማ የተሻለ እድል ከተሰጣቸው ግን ወደፊት ብዙ ሴቶችን በተለያዩ መድረኮች ላይ ማየት እንደሚቻል ገልጻለች።

ከነጻ ትምህርት እድል ጋር በተያያዘ አንድ ተሳታፊ የዊንሮክ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያን ልምድ አካፍለዋል። እንደተናጋሪዋ ዊንሮክ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ የሚያተኩረው በሴቶች ላይ በመሆኑ ለሴቶች የነጻ ትምህርት እድል በመስጠት ተሳክቶለታል ብለዋል። አክለውም እድሉ በ40% ከተወሰነ የነጻ ትምህርት እድሉ ሴት እጩዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችልና ውድድሩም እንደሚከብድ ገልጸዋል። ስለሆነም እድሉን ለሴቶች መስጠት ከተፈለገ 100% ለሴቶች ብቻ መሰጠት አለበት ብለዋል።

በሌላ በኩል አንድ ተሳታፊ በየትኛውም ደረጃ የሴቶችን ተሳትፎ የሚገድበው የጾታ ልዩነት ወይስ ድህነት ነው የሚለውን ጥያቄ አቅርበዋል። ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለዚህ ምላሽ ሲሰጡ የጾታ ልዩነት የሚጀምረው ከቤተሰብ መሆኑን ጠቅሰው እያንዳንዱ ሰው ቤተሰቦቹ ሲያሳድጉት ወላጆቹ የሚናገሩትን እያደመጠ እንደሚያደግና በኢትዮጰያዊያን ባሕል ወላጆች ወንዶች ልጆቻቸው ጉበዝና በራሳቸው የመተማመን ችሎታቸው የዳበረ እንዲሆን አድርገው ሲያሳድጉ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች አይናፋር እና ታዛዥ እንዲሆኑ አድርገው እንደሚያሳድጉ ገልጸዋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማንም ሰው የሴቶችን ንቁ ተሳትፎ ሊጠብቅ አይችልም። በተጨማሪም አንዳንድ ባሕላዊ ልምዶች በሴቶች ሥነ ልቦና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳላቸው ይህም አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ገለልተኛ እንዲሆኑ እንደሚያስገድዱም አብራርተዋል።

ሌላ ተሳታፊ እንደገለጹት በተለያዩ ጎጂ ልምዶች፣ የትምህርት እጦትና ድህነት ምክንያት ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩል ደረጃ ላይ አለመገኘታቸውን ገልጸዋል። በብዙ ሁኔታዎች ሴቶች በልጅነታቸው ትዳር እንደሚይዙና ለቤት ውስጥ ሥራዎች ሙሉ ኋላፊነት እንደሚሸከሙ ገልጸዋል። ሌላው ቀርቶ የራሳቸው ሥራ ያላቸው ሴቶች እንኳን ከሥራ በኋላ ቴሌቪዢን ለመመልከት፣ ሬዲዮ ለማዳመጥና ጋዜጦች ለማንበብ እድል የላቸውም፣ ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ ሥራ ሲወጠሩ ባሎቻቸው ግን ከጓደኞቻቸው ጋር የመጫወት ወይም ቴሌቪዢን የመመልከት እድል አላቸው በማለት ገልጸዋል።

አክለውም ከድሃ ቤተሰብ የተገኙ ልጃገረዶች ለሥራ ፍለጋ በሚያደርጉት ጥረት ለአስገድዶ መደፈር እንደሚጋለጡ ጠቅሰው እንዲህ አይነት ችግሮች ሕጻናቱን ወደ ሴተኛ አዳሪነት ይገፋፋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በቢሮዎች አካባቢም ከሴት ሠራተኞች ይልቅ የስልጠና እድልን ጨምሮ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞቸን የማግኘት እድል ቅድሚያ ለወንዶች ይሰጣል፡፡ አንዳንዴም ሴት ሠራተኞች ለስልጠና ስለሚያስፈልገው መመዘኛ እና ማን እድሉን እንዳገኘ ምንም ግንዛቤ የሌላቸው ናቸው፤ አለቆች ብዙውን ጊዜ ይሄንን እድል ለራሳቸው ጓደኞች ወይም ሊጠቅሙት ለሚፈልጉት ሰው እንደሚሰጡም ጨምረው አብራርተዋል፡፡

አንድ ተሳታፊ የትምህርትን ጠቀሜታ በማጉላት ለወ/ሮ ፀዳለ ያቀረቡት ጥያቄ የመድፈር ወንጀል የፈፀሙ ወንጀለኞችን በማስተማር ባህሪያቸውን መቀየር ወይስ ከባድ ቅጣት መወሰን ይመረጣል የሚል ነበር፡፡ በእኚሁ ተሳታፊ የቀረበው ሁለተኛው ጥያቄ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ሪፖርት ሲደርሳቸው ክበባቸው የሚሰጠውን የአገልግሎት አይነት ማብራሪያ እንዲሰጥበት የሚጠይቅ ነበር፡፡

ወ/ሮ ፀዳለ የቀረበውን ጥያቄ መመለስ የጀመረችው የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን ለመቀነስ የትኛው አማራጭ ተቀባይነት አለው በሚለው ነው፡፡ የወንጀለኞችን ባህሪ ለመቀየር ማስተማር ቀዳሚው ተግባር መሆኑን በመቀበል፣ ሊለወጡ ካልቻሉ ግን ለድርጊታቸው ከባድ ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባ ገልፃለች፡፡ ለምሳሌ ቁጥራቸው በዛ ያለ ወንዶች እድሜያቸው ከ7-8 አመት የሆኑ ልጆች መድፈራቸውን ገልፃ ይህን የሚፈፅሙ ወንጀለኞች ከ15 አመት በላይ የሆኑ ልጃገረዶችን ከደፈሩት ወንጀለኞች የበለጠ ከባድ ቅጣት ሊጣልባቸው እንደሚገባ ገልጻለች፡፡ በሌላ በኩል ከተሳታፊዎች መካከል ወንጀለኞችን በትምህርት መቀየር ይመረጣል የሚሉ ተከራካሪዎችም ነበሩ፡፡

ወ/ሮ ፀዳለ የኤች አይ ቪ ክበባቸው የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ ስትመልስ የአስገድዶ መድፈር ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ተጠቂዎቹን ወደ ሆስፒታልና ወደ ፖሊስ እንደሚልኩ ገልፃለች፡፡

ሌላ ተሳታፊም በፆታ ጭቆና ዙሪያ ያላቸውን ልምድ አካፍለዋል፡፡ ወጣት ልጃገረዶች ዛሬም ቢሆን እድሜያቸው ሳይደርስ ለጋብቻ እንደሚገደዱ እና እሳቸው ራሳቸው የ7 አመት ልጅ ስታገባ በግብዣ ስነስርአቱ ላይ መገኘታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ወጎች ይህንን መሰል ፆታዊ ጥቃትን ለማስወገድ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተሳታፊዋ ከሰርግ ጋር የተያያዙ ወጭዎች ከፍተኛ መሆናቸውንና ይህም የቤተሰብን ድህነት በማባባስ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ገልፀው ይህንን ለማስወገድ የተደረገን የህብረተሰብ ድጋፍ ተናግረዋል፡፡ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በጋብቻ ስነስርአት ወቅት ህዝቡ ከየራሱ ቤት ምግብና መጠጥ በማምጣት ይሰበሰባል፡፡ ተሳታፊዋ እንዳረጋገጡት ልምዱ የመቀጠል ሁኔታ እውነት ከሆነ ለድግስ የሚወጣውን ወጭ ስለሚያስቀር በተጋቢዎችና በቤተሰባቸው ላይ ያለውን ወጪ የሚቀንስ ይሆናል በማለት ይህ አይነት ድርጊት ሊበረታታ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም እያንዳንዱ አቅራቢ ማጠቃለያ እንዲሰጥ ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡ የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ድህነትን ለመዋጋት የትምህርትን አስፈላጊነት አስምረውበታል፡፡ በተጓዳኝ ወላጆች ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች እኩል የትምህርት እድል መስጠት እንዳለባቸውና የፆታ ልዩነትን ለማስወገድ ከቤተሰብ መጀመር እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ከማናቸውም ሙያ ሴቶችን የሚያገሉ ጎጂ ባህላዊ ልማዶች ሙሉ በሙሉ መወገድ አለባቸው፣ በዚህም ድህነትን ከሀገሪቱ ማስወገድና በአብዛኛው በሴቶች ላይ ሰፍሮ የነበረውን ድህነት መቀነስ ይቻላል ብለዋል፡፡

አቶ ተመስገን ከድህ ቤተሰብ የተገኙ ህፃናትን ለማስተማር ፕሮፕራይድ ያደረገውን ጥረት በተመለከተ በሰጡት አስተያየት በመጀመሪያ በአካባቢው ት/ቤት ለማቋቋም ያደረገው ጥረትና ያጋጠመውን እንቅፋት ጠቅሰው እንዲያውም ከአንዳንድ ተቋማት የፕሮፕራይድን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የተቃወሙ እንደነበሩም ገልፀዋል፡፡ ከድህነት ጋር የተያያዙ ችግሮች የሚቀረፉት ሙስና ከተወገደ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም የህይወት ልምዳቸውን ለማካፈል እድል የሰጧቸውን የመድረኩን አዘጋጆች አመስግነዋል፡፡

ወ/ት ኤልሳቤጥም አኮርድ ላደረገላት ድጋፍ ምስጋናዋን በመግለፅ ሌሎች ድርጅቶችም ተመሳሳይ ሙከራዎችን ማድረግ እንደሚገባቸው ገልፃለች፡፡

ወ/ሮ ፀዳለም ከድሀ ቤተሰብ የተገኙ ልጆች /እሷን ጨምሮ/ ከቤት ወጥተው ስራ ፍለጋ እንደሚሰማሩና ይህም ከድህነት የመነጨ መሆኑን፤ በቂ ገቢ ቢኖራቸው ኖሮ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ በቻሉ እንደነበር ገልጻለች፡፡ በተቃራኒው ከሀብታም ቤተሰብ የተገኙ ልጆች ለስራ ፍለጋ እንደማይጨነቁ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው ሁሉንም ፍላጎታቸውን ስለሚያሟሉላቸው ነው ብላለች፡፡ በመጨረሻም አሁን ለደረሰችበት ደረጃ እንድትደርስ ላበቃት ለፕሮፕራይድ ጥልቅ ምስጋናዋን አቅርባለች፡፡ በተመሳሳይ የመድረኩን አዘጋጆች ልምዷን ለማካፈል ለሰጧት እድል ምስጋናዋን አቅርባለች፡፡

በመጨረሻም ወ/ሮ ዘነበወርቅ አንድ ተሳታፊ መድረኩ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን በሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ ውይይት መካሄድ አለበት ላሉት የማህበራዊ ጥናት መድረክ በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚደረገው ውይይት በአዲስ አበባና በሌሎች ሁለት ክልሎች ለማካሄድ እቅድ እንዳለው ጠቅሰዋል፡፡ የማህበራዊ ጥናት መድረክ የዛሬውን አይነት መድረክ ሲያዘጋጅ ምንግዜም በሥርአተ ፆታና በልማት ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲሁም የስራ አጋሮቹንና ተባባሪዎቹን ለመጋበዝ /ለማሳተፍ/ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ እንደሚያደርግም ጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም ወ/ሮ ዘነበወርቅ በውይይቱ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች መድረኮቹ ሁልጊዜም ክፍት መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

# ድህነትና ሥርዓት-ፆታ

ጥሩወርቅ ዳንዶ
ገንዘብና ኢ ሚ ልማት ሚ/ር
ሴቶች ጉዳይ መምሪያ

## መግቢያ

ድህነት በኢ ሚ ቀውስ አስታ ሌሎችን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን እንዲናጋ የሚያደርግ ክስተት ነው። የኢ ሚው ቀውስ ደግሞ ከውጫዊ ጫናና ከውስጣዊ ችግር ጋር በተያያዘ መልኩ በአገርና በህዝብ ላይ ብሎም በግለሰብ ህይወት ላይ ነውጥንና ቀውስን ያስከትላል።

እ.ኤ.አ. ከ1980ዎቹ ወዲህ ካደጉት አገሮች የኢ ሚ እንቅስቃሴ ለውጥ የተነሳ ታዳጊ አገሮች በፖሊሲዎቻቸውና ዕቅዶቻቸው ላይ የውጭ ጫና አቅም እያሳጣቸው እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። በ70ዎቹ ዓመታት የተከሰተው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ብዙዎችን አገሮች ለጭማሪው የነዳጅ ወጪ መሸፈኛ ዕዳ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። ከዚህም የተነሳ ብዙ ታዳጊ አገሮች ከግል አበዳሪዎችና ከዓ ለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እየተበደሩ ዕዳውን ከፍለው ሳይጨርሱ የወለድ ጫና እየበዛባቸውና ከውጪ የሚያስገቡት ዕቃ ከፍተኛ ዋጋ ሲጠይቅ ወደ ውጪ የሚልኳቸው ዕቃዎች ዋጋ አነስተኛ በመሆኑ የመግዛት አቅማቸው ተዳክሞ ከወቅቱ የቴክ ሎጂ ዕድገት ጋር መራመድ ስለአቃታቸው ህዝባቸው በድህነት አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ይህንን ለመካላከል ሲባል የመዋቅር ማስተካከያ መርሀግብሮች ተቀረጸው እየተተገበሩ ያለ ሲሆን፣ ውጤቱ ጾታዎች በእኩልነት ልማት ላይ እንዳይሳተፉ ጫና ማሳደሩ እየታየ መጥቷል። በተለይም በሴቶች ላይ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጉዳቶችን እያዳረሰ ይገኛል። ለምሳሌ የምግብ ሸቀጦችን ከውጪ ለሚያስገቡ አገሮች ዋጋ ሲጨምር ምግብ ለቤተሰብ የማቅረብ ኃላፊነት የሴቶች ይሆንና ተጨማሪውን ዋጋ ለማካካስ ሴቶች ገንዘብ ስለማይ ራቸው ስጋት ውስጥ ይከታቸዋል። ይህ ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ የምግብ እጥረት እንዲ ርና አጥቢ እናቶች፣ ነፍሰጡሮችና ህፃናት ለበለጠ ጉዳት እንዲጋለጡ ሚና ይጫወታል።

የመዋቅር ማስተካከያው ከመንግስት ለመ ሪያ ቤት፣ ለትራንስፖርት፣ ለህፃናት እንክብካቤ፣ ለጤናና ለትምህርት የሚደረገውን ድጎማ ስለሚያስቀር በዚሁ መዋቅር ማስተካከያ ሳቢያ የትኛውም የመንግስት በጀት ቅነሳ ጫና የሚያርፈው በሴቶች ጫንቃ ላይ እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ይህ ደግሞ የሥርዓት-ፆታን እኩልነት ወደ መጣስና ብሎም ሰብዓዊ መብትን ወደመጋፋት ያመጣል።

ሥርዓት-ፆታ ማለት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ ግንኙነት ከባህልና ከህብረተሰብ ህግጋት አኳያ የስራ ክፍፍል ምን መምሰል እንዳለበት የሚያሳይ ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜና ከባህል ባህል የሚለዋወጥ ነው። የሥርዓት-ፆታ ጉዳዮች በልማት ሂደት ውስጥ ካልተካተቱ የአንድ አገር ዕድገት ምንም ያህል ዕድገት ሊያሳይ አይችልም። በተለምዶም የሥርዓት-ፆታ ጉዳይ የሴቶች ድርሻ ብቻ ተደርጎ ስለሚወሰድ ጉዳዩ የልማት ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ መፎካከሪያ የሆነ ይመስላል። መሰረታዊ ሃሳቡ ሲጠና የሁሉም ዜጋ ስለሆነ ሁሉም በጋራ ችግሩን ለመግታት መንቀሳቀስ ድህነትን አስወግዶ የአገርን ዕድገት ለማፋጠን ይረዳል። ሴቶች በልማት ላይ አስተዋጽኦ እንዲ ራቸውና የልማት ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተፈለገ በቤተሰብ፣ በህብረተሰብ እና በአገር ደረጃ የውሳኔ ሰጪነት ሚናዋ እንዲያድግ ማድረግ ብቸኛና የመጀመሪያ እርምጃ ሊሆን ይገባል።

***ድህነት ምንድን ነው?***

*ድህነት ከአገር ኢ ሚ አኳያ ስንመለከተው አንዲት ሀገር ከአገር ውስጥ ምርት እንቅስቃሴና ከውጪ ግብይት የምታገኘው ገቢ ወጪዋን መሸፈን ሳይችል ቀርቶ በየጊዜው የልማት እንቅስቃሴዋን በብድርና በችሮታ ወደምትደገፍበት ደረጃ ስትደርስና ከዕዳ ነፃ መሆን ሳትችል ስትቀር፣ ዜጎቿ ሀብቷን እኩል ለመጋራት ሳይችሉ ሲቀሩና ያላትንም የሰው ኃይል በተገቢው የልማት ዘርፍ ማሰማራት ሳትችል ቀርታ ተመጽዋችና ደካማ፣ ተመሪና ተገገር ወደ መሆን ስታመራ ነው። መለኪያውም በአገር ደረጃ ለማህበራዊ ልማት የምታውለው የበጀት መጠን፣ ዓ መታዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ፣ እናቶችና የህፃናት ጤና፣ የህብረተሰብ የእድሜ ጣራ የገቢና የወጪ ንግድ ሚዛን፣ የዕዳ ጫና ወዘተ ይሆናል።*

*የአንድን ሰው ድህነት ደግሞ በገንዘብ ምንጭ እጦት፣ ማህበራዊ የሆነ ግንኙነት እጥረት፣ ራስን ለማሻሻል በአቅም ውስን መሆን፣ የጊዜ እጥረት፣ የቋሚ ንብረት ባቤት አለመሆን፣ የሙያና ዕውቀት እጥረት፣ ማህበራዊ ተቋማትን እጦት፣ በራስ ላይ ሆነ በንብረት ላይ የማዘዝና የመቆጣጠር ስልጣን ማጣት፣ ራስን አለመቻል፣ ጉልበት ከማጣት የተነሳ ጥገኛ መሆን፣ የመንፈስ ጥንካሬ ማጣት በአጠቃላዩ ለኢ ሚያዊ፣ ለፖሊቲካዊና ለማህበራዊ ችግሮች የተጋለጠበትን ደረጃ በማስላት ማግኘት ይቻላል። ይህ ደግሞ የአገርን ሀብት ለመጋራት ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢ ሚያዊ ሁኔታዎች ከመጓደላቸው የተነሳ ሊፈጠር የሚችል ክስረት ሲሆን ውጤቱ ዜጋን በእኩልነት ያለማየት በጥልና በክርክር ሰላም ማጣት፣ አንዱ በሌላው መበዝበዝን በበታችነት ስሜት መ ርን ጎልቶ እንዲወጣ ያደርጋል።*

*የድህነት ትርጉም አንዱ ከሌላው ጋር እርስ በእርሱ የተቶራኘ ከመሆኑ የተነሳ የማህበራዊ ጉዳይ ድህነትን መለኪያ ከኢ ሚያዊው የድህነት መለኪያ ጋር ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ የተያያዘ ሲሆን እንደየአገሩና እንደየአካባቢው የህብረተሰቡ የአኗኗር ደረጃ ይተረጎማል/ይለያያል። ለምሳሌ በዓለም ደረጃ ብንመለከት በአውሮፓውያኑ አገር የድህነት መለኪያው ከአሜሪካ ቹ፣ የሩቅ ምስራቅ አገሮች ከአረቦቹ፣ የላቲን አሜሪካ ቹ ከአፍሪካውያን በዓይነቱና በደረጃው ይለያያሉ። የአፍሪካን አገሮች እንኳን ብናይ የሰሜን አፍሪካ አገሮች ከደቡብ አፍሪካ፣ የምስራቁ ከምዕራቡ እንዲሁ ይለያያል። ዳሩ ግን በአገሮች መካከል ለሁሉም አማካይ የሆነ የድህነት መለኪያ መጠን ተበጅቶለታል። ወደ አገራችንም ስንመጣ እንደየክልሉ ህዝብ አኗኗርና እንደገበሬው አገላለጽ የድህነት መለኪያ ዓ ይነትና ይዘት ይለየያል። በደቡብ ክልል ድሀ የሚባለው ገበሬ አንድ ጥማድ በሬ፣ ሁለት ሄክታር መሬት አንድ የወተት ላም ወዘተ ያለው ቢሆን የምእራባዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬዎች የድህነት መለኪያቸው ሌላ ሊሆን ይችላል።*

*የአንድ ሀገር የህብዝ ብዛትና የምርት ዕድገቱ ተመጣጣኝ ሳይሆን ሲቀርና በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ከሚሳተፈው ይልቅ ጥገናው ሲበዛ፣ ወደ መንግስት ካዝና ከሚገባው ገቢ ወጪ የሚደረገው ሲበዛ፣ ከአቅም በላይ የሆነ የቅንጦትና የምቾት ፍላጎትን ለማሟላት ጥረት ሲ ር የሚመረተው ምርት የህዝብን ፍላጎት ስለማያሟላ የልማት አውታሮች ማነቆ ይበዛባቸዋል። ይህ ማለት የመንግስት የገቢ ምንጭ ለተጨማሪው የህዝብ ብዛት የጤና ተቋማትን፣ ት/ቤቶችን፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትንና የከተማን እና የገጠርን ህዝብ የኑሮ ደረጃ ለማቀራረብ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ መንገድና መብራት ለማዳረስ ከፍላጎት አድማስ መስፋት አኳያ የአቅርቦት ምንጭ ውስን ይሆንና ስራ አጥና ተመጽዋች ዜጋ በዝቶ በአገር ደረጃ የጤንነት፣ የአመጋገብ፣ የማህበራዊ ግንኙነት፣ የትምህርት ወዘተ መለኪያ ደረጃ መሆን ከሚገባው በታች እያሽቆለቆለ እንዲሄድ ያደርጋል። አገሪቱንም ድሃ የሚል ስያሜ እንድታገኝ አስተዋጽኦ ይ ረዋል።*

### አገራችንን ለድህነት ከዳረጉ ችግሮች ዋናዎቹ፦

- የውጭ እዳ ጫና፣
- ተደጋጋሚ ድርቅና ተደጋጋሚ ጦርነት (ለስደትና ለንብረት መውደም የዳረገ)፣
- ከሀብታችንና ካለን የመጠቀም አቅም ጋር ያልተመጣጠነ የህዝብ ብዛት ናቸው።

### የድህነት ምክንያት በከተማ ውስጥ፦

- የቤት እጦት፣
- የገቢ ምንጭ ማጣት፣
- የባንክ ብድር ለማግኘት ብቁ አለመሆን፣
- ከማን አንሼ የድግስ ወጪ፣
- የልጅ ብዛት ለመጦር ለመለመኛነት ወዘተ…

### የድህነት ምክንያት በገጠር፦

- የመሬት ባለቤት አለመሆን፣
- የእርሻ መሳሪያ ማጣት (በሬ፣ ሞፈርና ቀንበር፣ ማዳበሪያ፣ ዘር)፣
- የወተት ከብት አለመ ር (ፍየልና ላም)፣
- ከእርሻ መሬት በቂ ምርት አለማግኘት (ከኋላ ቀር የአስተራረስ ዘዴ የተነሳ)፣
- የምርት ውጤትን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ የሚያስችል የተደራጀ ገበያ፣ መንገድና ትራንስፖርት አለመ ር (ከወንድ በበለጠ ሴትን ሸክም ተሸክማ ረጅም መንገድ እንድትጓዝ ያደርጋታል)፣
- ትምህርት ቤትና የጤና ተቋማት አለመ ር፣
- ንፁህ ውሃ አለማግኘት፣
- ወዘተ…

### ሥርዓተ-ፆታና የልማት ግንኙነት፦

ሥርዓተ-ፆታና ልማት ማለት ትምህርት፣ ጤና፣ ማህበራዊ አገልግሎት፣ መሰረተ ልማት፣ የውሳኔ ሰጪነት ስልጣን የተሰሚነት ጉዳይ ወዘተ ለሴትና ለወንድ በተገቢውና ለእያንዳንዱ ሊደርሰው እንደሚገባ እንዲሳተፉና ውጤቱንም ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲጋሩ የማድረግ ሂደት ነው።

ሴቶችና ወንዶች በትምህርት እኩል ካልተሳተፉ በህብረተሰቡ ውስጥ የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ይመጣል ይህም የአገሪቱን የምርት እድገት ሩጫ እንዲያዘግም ያደርጋል። በተጨማሪም የሴት ልጅ አለመማር የውልደት ብዛትን ይጨምራል፣ የህዝብ ብዛት ያለገደብ እንዲሆን ይረዳል፣ ቤተሰብ ኑሮውን ለመምራት ካለመቻሉ የተነሳ የህፃናትን ጉልበት ወደመሸጥና መበዝበዝ በተለይም ሴቶች ህጻናት ገላቸውን ወደ መሸጥ እንዲያመሩ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የህዝብ ሙብዛት ከቤተሰብ የገቢ ምንጭ ዕድገት ጋር ካልተጣመረ ለሴት ልጅ አኗኗር አመቺ አይሆንም ማለትም ቤተሰብ ሆነ ህብረተሰብ የችግርን ቀንበር በሴቷ ላይ ጭ ዝም ስለሚል የአገር እድገት ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

ሌላው መታየት ያለበት ጉዳይ ሴቶችና ወንዶች ለልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉበት ሴክተር ውስጥ እንደሚገባው መሰባጠራቸውን ማረጋገጥና የወደፊት የአገር ራዕይን በዚህ አቅጣጫ ማስተካከል ያስፈልጋል። ምክንያቱም የእያንዳኑ ሴክተር ዕድገት ከወንድና ከሴት የተለያየ የስራ ጊዜንና ድርሻን እንደሚፈልግ በመገንዘብ በዓላማ ማቀድ አስፈላጊ ይሆናል። በሙሉ

ጉልበት ተግባር ላይ ለመሳተፍ ማን የጊዜ እጥረት እንደሚገጥመው ታውቆ ሁኔታን ለማሻሻል ማቀድን ይፈልጋል።

በጾታዎች መካከል እኩል የትምህርትና የስልጠና ዕድል አለማግኘት በተለይ የሴቷ አለመማር ለህዝብ ብዛት፣ ለዝቅተኛ መዋዕለንዋይ ተግባር፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረትን ሲያመጣ እነዚህ ሁሉ የአገሪቱን የልማት እድገት እንዲቀንስ አስተዋጽኦ አላቸው። የሴት ልጅ ትምህርት በከተማ ሆነ በገጠር ሲታይ ከገቢ እጦት ብቻ ሳይሆን የማህበራዊና ባህላዊ አስተሳሰብ ጫና ጭምር ነው።

የሴት ልጅ መማር ከጤና ጋር ስናያይዘው የጋብቻ ዕድሜ ከፍ ያለ ይሆንና የልጅ ብዛት እንዳይ ር ይከላከላል። በአመጋገብ በቂ ገቢ ስለሚ ራቸው የተመጣጠነ ምግብ ይመገባሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ የጨቅላና የህፃናት ሞት ይቀንሳል የእናቶች በወሊድ መሞት ይቀንሳል የህዝብ ብዛት ከአገሪቱ የማስተዳደር አቅም ጋር ይመጣጠናል ለኢ ሚው ልማት ዕድገት በማህበራዊ ዘርፍ እንቅስቃሴ ከፍ ያለ ሚና ይጫወታል።

የገቢ ምንጭ እጦት፣ የተሰሚነት ዕድል ማጣት፣ ከቤተሰብ እስከ መንግሥት መዋቅር በውሳኔ ሰጪነት አለመሳተፍ፣ ወዘተ በሴቶች ላይ የኃይል ጥቃት እንደሚፈጸምባቸው ያደርግና በጤናቸው ላይ ቀውስን ያመጣል። ይህ ደግሞ የህብረተሰቡን የጤና መመዘኛ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲሆን ያደርጋል። ለምሳሌ ተገድደው ይደፈሩና ለኤድስና ጥንቃቄ ለጎደለው ውርጃ ተዳርገው ይሞታሉ፣ በባሎቻቸው ተደብድበው አካለ ጎዶሎና እንዲሁም ህይወታቸውን እስከማጣት ይደርሳሉ በግርዛት ምንም ዓይነት ጉዳት የማያመጣውን አካላቸው ተቆርጦ ይወድቅና በወሊድ ጊዜ ለማይገባ ደም መፍሰስና ሞት ይዳረጋሉ።

በአገራችን የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ጋር ሲተያይ ለ100 ወንዶች 101 ሴቶች እንደሚሆን በጥናት ተደርሶበታል። ይህ ደግሞ የሴቱ ቁጥር ከወንዱ ይልቅ እየበዛ እንደሆነ ያመለክተናል። ለዚህም ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ጥቂቶቹ የጦርነት መደጋገም፣ ወንዶች ስራ ፍለጋ ወደ በረሀማ አካባቢ በመሄድ ለወባና ለሌሎች ገዳይ በሽታዎች መጋለጥና ወጣት ሴቶች በዕድሜ ለሚበልጧቸው በመዳር ባሎቻቸው አርጅተው ሲሞቱ ሴቶቹ በህይወት የመቆየትና በሌሎችም ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችል ይገመታል። ሴቶች በማህበራዊ ልማት ሆነ ኢ ሚያዊው ልማት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ሆነው ሳለ ከባህል ተጽዕ የተነሳ በስራ ስምሪት በውሳኔ ሰጪነትና አስተዳዳሪነት ደረጃ ቁጥራቸው አናሳ ይሆንና በንዳና ተዳዳሪዎች፣ በተራቡ፣ በታመሙት፣ በአካል ስንኩሎች፣ በአቅመደካሞች፣ በድምጽ የለሾች፣ በመሬት የለሾች፣ በለማኞች፣ በስደተኞችና በአገር ለአገር ተንከራታቾች መሀል ቁጥራቸው ብልጫ እንዳለው ከዕለታዊ እንቅስቃሴ እይታ እውነተኛውን ስዕል ማየት ይቻላል። ይህ ደግሞ ከሀገር የልማት ጉዳይ ጋር አያይዘን የተመለከትነው እንደሆነ ያለንን የሰው ኃይል በአግባቡ ካለመጠቀማችን የተነሳ ምን ያህል በድህነት ባህር ውስጥ እንደወደቅን በግልጽ ያሳየናል።

ከላይ በተብራሩት ጉዳዮች ድህነት የልማት እንቅስቃሴዎች ክስረትን እንደሚያመለክት መረዳት ችለናል። በልማት እቅድ ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን ዘርዝሮ በበጀት በተደገፈ መልኩ መስራትና በጾታዎች መካከል ያለውን ክፍተት ለማስቀረት መታገል የልማት ሚዛናዊነትን በመጠበቅ የዘቀጠውን የህብረተሰብ ክፍል እንድንጠቀመውና ትርፍ አምራች እንድንሆን ይረዳናል። በዚህ ዙሪያ ልንጠነቅቅለት የሚገባን የሴቶች ሰብአዊ መብቶች በቀላሉ የሚጣሱበትና በግድየለሽነት የሚታዩበት ሁኔታዎች በስፋት ካሉ ሴት ከልማት እንቅስቃሴ ተገልላ የእኩልነት ሚዛኑ ሊዛባ እንደሚችል ነው። "ልማት ወይንም ዕድገት ማለት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን የሰዎችን አእምሮአዊ፣ አካላዊ

ማህበራዊ ደህንነት መስተካከልና መሟላት ጭምር ነው።[1] እንግዲያውስ ይህንን እውነታ የምናምን ከሆነ የመብቶች መከበር ለልማትና እድገት ሂደት አስፈላጊ የሆነ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ልንቀበል ይገባል።

በአገራችን የሴቶች መብቶች እንዲከበሩ በመጀመሪያ ቀደም ብለው የወጡትን መመሪያዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን ወዘተ... ማሻሻል፣ አዲስ የሚወጡትንም ቢሆን የሴቶችን መብቶች የሚጻረሩ ባህላዊ አመለካከቶችና ድርጊቶችን፣ ደንቦችንና ህጎችን፣ ለመከላከል በሚያስችል መልኩ መቅረጽ እና ተፈጻሚነታቸውን መከታተል፣ ለሚደርሰውም ክስረት/ጉዳት ተጠያቂ እንዲ ር በማድረግ፣ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የውሳኔ ሰጪነት ሚና እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል። በእርግጥ በአገራችን ት/ቤቶች ከወትሮው በበለጠ በየቦታው ተከፍተዋል ዳሩ ግን ሴት ልጅን ከጠለፋና ከአስገድዶ መድፈር የሚያስጥሉ ሁኔተዎች ከሌሉና የት/ቤት ጊዜዋን የሚሻሙ የስራ ጫናዎች ካልተቀነሱ በክፍል ደጋሚዎች መካከል የሴቶች ቁጥር መብዛትና ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ በኋላ የሴቶች ቁጥር አናሳ እንዲሆን ያደርጋል።

### የሴቶችና የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ

| ክልል | ጠቅላላ የባለ ይ ታ ብዛት | ወንድ | | ሴት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ከመቶ | ብዛት | ከመቶ |
| አማራ | 2,583,800 | 2,139,600 | 83 | 444,200 | 17 |
| አፋር | 28,260 | 26,050 | 92 | 2,210 | 8 |
| ኦሮሚያ | 3,312,930 | 2,751,100 | 83 | 561,830 | 17 |
| ጋምቤላ | 23,870 | 18,700 | 78 | 5,170 | 22 |
| ደቡብ | 1,960,410 | 1,615,800 | 82 | 344,610 | 18 |

*በግብርና ሚኒስቴር ሴቶች ጉዳይ የተዘጋጀ የጾታና ልማት መመሪያ ገጽ 10

## ሴቶችና ትምህርት

### በመንግስትና የመንግስት ባልሆኑ የአንደኛ ደረጃ (1-8) ት/ቤቶች የተማሪዎች ብዛት በጾታ

| ዘመን | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ | የሴቶች % |
|---|---|---|---|---|
| 1986 | 1,602,282 | 1,038,784 | 2,641,066 | 39.33% |
| 1993 | 4,346,864 | 2,927,257 | 7,274,121 | 40.24% |

### መንግስትና የመንግስት ባልሆኑ የሁለተኛ ደረጃ (9-12) ት/ቤቶች የተማሪዎች ብዛት በጾታ

| ዘመን | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ | የሴቶች % |
|---|---|---|---|---|
| 1986 | 195,625 | 161,569 | 357,194 | 45.23% |
| 1993 | 389,601 | 259,620 | 649,221 | 39.99% |

### በዩኒቨርስቲዎችና በ ሌጆች የዲግሪና የዲፕሎማ የተማሪዎች ብዛት በጾታ

| ዘመን | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ | የሴቶች % |
|---|---|---|---|---|
| 1986 | 13,290 | 2,148 | 15,438 | 13.91% |
| 1993 | 37,121 | 9,691 | 46,812 | 20.70% |

ምንጭ፡ በትምህርት ሚ/ር አመታዊ የስታትስቲክስ ጭምቅ 1986፣ 1993

[1] ግብርና ሚኒስቴር በሴቶች ጉዳይ የተዘጋጀ የጾታና ልማት መመሪያ ገጽ 1

የኢ ሚያችን ዋነኛው የልማት አውታር ግብርና ሲሆን በግብርናው መስክ የሴቶች ድርሻ የጓሮ አትክልት ማምረት፣ ከቤተሰብ እንክብካቤ አልፈው ሞፈር ቀንበር ይዘው ከወንዱ ጋር ማሳ ወርደው መጎልጎል ፣ ማረም፣ መ`ከር ስብሰባ፣ አውድማ ከማዘጋጀት እስከ እህል ማከማቸት ከቦታ ቦታ መጠኑ ቢለያይም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በከብት ዕርባታውም እንዲሁ ድርሻ ሲ ራቸው በተጨማሪ የቤተሰብ የገቢ ምንጭ ለማዳበር ልዩ ልዩ ተግባራትን እንደፈትል፣ እንደስፌት፣ ችርቻሮ ንግድ ያከናውናሉ። በጥቅሉ በኢትዮጵያ 35-50% የእርሻ ስራ የሚያከናውኑት ሴቶች እንደሆኑና በአጠቃለዩ በእርሻ፣ በከብት እርባታና ሌሎች ግብርና ነክ ስራዎች ከ50-60% በሴቶች ይከናወናሉ። (CERTWID INFORMS Vol. 6, No. 1 Page 16) ዳሩ ግን ከእርሻ የተገኘውን ውጤት ከወንድ ጋር በጋራ ተወያይቶ በመወሰን ረገድና ድርሻን ከማግኘት አኳያ በባል ውዴታና ፈቃድ ላይ የተጣለ ሲሆን የስራ ጫናዋንም ለመቀነስ ቢሆንና ኑሮዋን ለማሻሻል ስለመጋቢ የገጠር መንገዶች ስለወፍጮ፣ ስለውሃ ስለት/ቤት ስለመብራት ወዘተ ፍላጎቷን ማማከር የሚሰሩበት ባህል አልዳበረም። አንዳንድ አካባቢዎች ላይ እነደ ወፍጮ እንደ ውሃ ቧንቧ በዘላን አካባቢ ደግሞ የት/ቤት ግንባታ ወዘተ ምክክሩ ላይ ባለመሳተፉቸወ ለተፈላጊው ጥቅም ያልዋሉበትና የሚበላሹበት ሁኔታ አመዝ ይገኛል።

በንግዱም ዘርፍ ብንሄድ ሴቶች ከጥቃቅንና መካከለኛ የንግድ ዘርፍ አልፈው በጅምላ አስመጪና ላኪ ንግድ ሲሳተፉ እምብዛም አይታይም ምክንያቱም የመሬትና የቤት ባለቤትነት ጉዳይና አለመማርም የብድር ገንዘብ እንዳያገኙ ተጽእ ያደርጋል። ይህ ደግሞ የንግዱን ዓለም ለማወቅና ለመለማመድ አየስችልም። በአገራችን ከምናየው ተጨባጭ ሁኔታ ከድህነት ለማላቀቅ ማስፈለጉን አምነን በኢ ሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊና በባህላዊ የአኗኗር ዘይቤአችን የሴቶች የመብት ጥያቄ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባ ሆ አቅሚንም ማጎልበት ወሳኝ ይሆናል። ለዚህም አገራችን ያመነችበትንና ያጸደቀችውን የ1995 የቤጂንግን ስምምነት እና ሌሎችንም በሴቶች ዙሪያ የፈረመቻቸውን ውሎች በተግባር መተርጎም ይጠይቀናል። ሴቶችና ወንዶች በሁሉ መስክ እኩል መብት ሊ ራቸው ካልቻለ ለድህነት ምክንያት ለሚሆኑ ነገሮች በር ይከፈትለታል። በጦርነት ጊዜ ከወንዶች ይልቅ ለአደጋ መጋለጥ፣ በድርቅ ጊዜ የቤተሰብን ምግብ ከማሰናዳት አኳያ ከእህል ጉድለቱ የተነሳ መታወክ ካለመማርና በንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ከማጣት የተነሳ ለሴተኛ አዳሪነት፣ ለስራ አጥነት፣ ለስደት መጋለጥ ወዘተ ያስከትላል። ይህ ሁኔታ እየተከሰተ ያለው በቤተሰብ ሆነ በህብረተሰብ አስተዳደር መርሆዎች የባህሉ ተጽእ ስውር በሆነ መልኩ እየተገለጸ ቅን አስተዳደርን ስለሚሸረሽረው፣ ተጽእ ውን ለመቅረፍ ገና ጨቅለዎች በእናቶቻቸው እቅፍ እያሉ በምን መልኩ መታነጽ እንደአለባቸው ህብረተሰቡን በተለያዩ ዘዴዎች በማስተማር እና በት/ቤት ዙሪያ ያለው ስራ ማለትም ከካሪኩለም አዘገጃጀት ጀምሮ እስከ መምህራን ምልመላና ስልጠና በስርዓተ-ጾታ መነጽር መታየት ግድ ይላል። በየአስተዳደሩ መዋቅር የአፈጻጸም ግድፈት እንዳይ ር የተጠያቂነት መረብ በጥንቃቄ መዘርጋት፣ ፖሊሲና አዋጆችን ተከትሎ የአፈጻጸምና የክትትል መመሪያዎች በማውጣት የባህልን ተጽእ ከህብረተሰቡ ውስጥ ለመቅረፍ ሙሉ ዝግጅት ይጠይቃል። በዓለምና በአገር አቀፍ የኢ ሚ ቀውስ ጊዜ የግል ድርጅቶች በቅድሚያ የሚያሰናብቱት ሴቶችን ሲሆን፣ በኃይል ጥቃት ዙሪያ ከቤተሰብ እስከ ህብረተሰብ ያለምንም ተከላካይ ለድብደባ እና ለአስገድዶ መድፈር፣ በጦርነት ወቅት ያለፍላጎቷ መደፈርና ከህጻናት ጋር መሰደድ እና ህጋዊ መብትን እንኳን ለማስከበር በምታደርገውም ትግል ፍትህ ሳታገኝ የምትንገላታ ሴት መሆኗ የተረጋገጠ ነው።

ዋሽንግተን የሚገኘው Population Reference Bureau በ2002 ባወጣው ዓ ለም አቀፍ የሴቶች ሁኔታ በሚል ርዕስ ስር በዘረዘረው ስለአገራችን ሴቶች ሲገልጽ የሴቶች ብዛት ወደ 33.2 ሚሊዮን፣ በ100 ወንዶች መካከል 101 ሴቶች እነደሚ ሩ፣ የዕድሜ ጣሪያ ለሴት 53 ለወንድ 51 የወሊድ ብዛት 5.9 እነደሚሆን፣ ዘመናዊ የወሊድ መከላከያ የሚወስዱት 6%፣ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶች ከ100,000

ሴቶች ውስጥ 1,800 እንደሚሆኑ፣ በመውለድ ዕድሜ ውስጥ ሆነው በHIV/AIDS የተያዙት 10.6% በመውለድ እድሜ ያሉት ደግሞ 14.9 ሚሊዮን እንደሆኑና ካለው ሴት ውስጥ 59% በስራ የተሰማሩ ሲሆኑ ከወንዱ ግን 86% እንደተሰማራ፣ በውሳኔ ሰጪነት ቦታ በፓርላማ ውስጥ 8% ሴቶች ሲሆኑ በሚኒስትሮች ካቢኔ ውስጥ 14% ሴቶች እንደሆኑ ያስረዳል።

ሌላው በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሴቶች ጉዳይ መምሪያ እ.ኤ.አ. 1999 ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሴቶች መረጃ በዘረዘረ መጽሄት ላይ የሰራተኛ ሴቶችን ደረጃ በደመወዝ ሲዘረዝር በሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ውስጥ 1800 ብርና ከዚያ በላይ የሚያገኙ ሴቶች 2% ብቻ እንደሆኑና ብር 105-199 የሚያገኙ 13% እንደሚሆኑ ሲገልጽ፣ የተቀሩት በነዚህ መሃል እንደሆኑ ያስረዳል። ይህም አብዛኛው ሴት በገቢ ደረጃ ዝቅተኛ ሁኔታ ውስጥ እንደሆኑ የሚያስረዳ ሲሆን በስራ ዓይነት ሲታይ ፕሮፌሽናል ሳይንስ 5% ሲሆኑ ክለርክና የጉልበት ሰራተኞች 20% እንደሆኑ ያመለክታል። በሁለቱም መረጃ ላይ ለሚታየው ክፍተት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ዝርዝር ጥናት ባይ ረውም የመማርና የስልጠና እድል ካለማግኘት እንደሚመጣ መገመት አያዳግትም።

ሴቶች አምራች ብቻ ሳይሆኑ በተፈጥሮ የሰው ማምረቻ ፋብሪካና የማሰልጠኛ ማእከል መሆናቸውን በመገንዘብ በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የተለየ ትኩረት ሰጥተን ከባህል ተጽእ  አላቅቀናቸው በሙሉ ኃይልና ጉልበት ወደ ልማት አቅጣጫ እንዲያመሩ ማድረግ ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ሲሆን ውጤቱን ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማየት አይቻልም። ይህ ደግሞ ተስፋ ሊያስቆርጥና፣ ዛሬ አቅም የለንም ወደምንልበት እንድናመራ ሊያደርገን አይገባም። ምክንያቱም ለውጡ አዝጋሚና ሁለንተናዊ ስለሆነ መሰረታዊ ለውጥን ለአንዴና ለመጨረሻ ለማምጣት፣ ለገበሬዋ ሴት ሆነ ለከተማዋ የቤት እመቤት ጉልበትና ጊዜ የሚጨርሰውን የቤት ውስጥ ስራ ማቃለያ ቴክ ሎጂ እንድትጠቀም በማድረግ በቀን ውስጥ ከ13 ሰዓት በላይ እየሰራች በጊዜ እጥረት እንዳትደክም በቂ የእረፍት ጊዜ  ሯት ጉልበቷን ሙሉ በሙሉ በምርት ተግባር ላይ አውላ የተሻለ ምርት በብዛትና በጥራት እነዲገኝ ማድረግ በዕድገት አቅጣጫ ትርፋማነቱ ያመዝናል። ምክንያቱም በረጅም ዕቅድ ውስጥ የሚገኘው የምርት ውጤት የቀደመውን ወጪ ይሸፍናል። በመሰረቱ በግብርናው ዘርፍ የሴቷን ድርሻ አጥርቶ ለመለየት እና ምን ቢደረግ ምርት ሊያድግ እንደሚችል ለማወቅ ወደየገጠሩ መንደሮች ገባ ብሎ የቤተሰብን አኗኗርና እለታዊ የስራ እንቅስቃሴ ማጥናት ያስፈልገዋል። ለሴት ልጅ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ በምርምርና ጥናት ላይ የተሰማሩት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለግብርና ዘርፍ የሴቶች ድርሻ ትኩረት ሰጥተውበት የመፍትሄ ሀሳብ ለማፍለቅ አልተጨነቁበትም። ግብርናው ላይ ሴቶች ካላቸው ጠቀሜታ አኳያ ይህ የልማት ክፍያ ዘመናዊነትን በያዘ መልኩ የምርት ውጤትን ከፍ ለማድረግ ሴቷን ሳያገልል ለውጥ ሊካሄድበት ይገባል። በተለይም አሁን ስትራቴጂ የተቀረጸለት የግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት ወንዶችን ወደከተማ እንዲፈልሱ እድል ከፍቶላቸው ሴቶችን ከህጻናቶቻቸው ጋር ገጠር እንዳያስቀራቸው ለመከላከል የሚያስችል በጥናት የተደገፈ ሁለቱን ጾታዎች በእኩልነት ለማስተናገድ በሚችል ዘዴ ዕቅድ ማውጣት ያስፈልጋል።

## ሴቶችን ከወንዶች ይልቅ ለችግር/ለድህነት እንዲጋለጡ አስተዋጾ የሚያደርጉ ጉዳዮች

- ሴትን የበታች የሚያደርጉ ልማዳዊና ባህላዊ የህብረተሰብ አስተዳደር ህጎች፦ ግርዛት፣ ጠለፋ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የውርስ ጋብቻ፣ የልውጫ ጋብቻ፣ ጋብቻ ላይ ጋብቻ፣ በንብርት ለውጥ ጋብቻ፣ የመሬት ይ ታ ባለቤትነትን የሚያግድ ስርዓት፣
- የመማር ዕድል አለማግኘት፣

- ከህብረተሰባዊ ተሳትፎ መታገድ/ማጀት ውስጥ መወሰን/በባልዋ ወይንም በወንድሟ በኩል ሀሳቧን ማስተላለፍ፣ በህግ ከለላ ሳይሆን በአባት በወንድምና በባል ከለላ ስር መሆን፣
- ጊዜን የሚሻማ ሁኔታና ጫና መብዛት፣
- በምርት ውጤት፣ በማምረቻ መሳሪያ፣ በስነ-ተዋልዶ ጤና የመወሰን ስልጣን ማጣት፣ የማምረቻ መሳሪያና የመሰረተ-ልማት አለመሟላት።

**መፍትሄው ምንድነው?**

ፍትህን ለማምጣት ለሴቶች እንቅፋት የሆኑትን ጎጂና ልማዳዊ አስተሳሰብ የሚያስወግድ ከቤተሰብ እስከ ከፍተኛ የስራ አመራር አካላት የሚነካ ደንብ ማውጣትና ተፈጻሚነቱን መከታተል፣ ትምህርትን ለማበረታታት ከመዋለ ህጻናት እስከ ከፍተኛ ተቋማት፣ ሴትን በኃላፊነት መመደብ የትምህርት ካሪኩለም ማሻሻል በፓርላማ ውስጥ ባለሙያና ቆራጥ ሴቶች እንዲገቡ ጥረት ማድረግ የመጀመሪያ እርምጃ ሲሆን በሌሎችም የልማት ተቋማት በብዛት ቆራጥ ባለስልጣናት ሴቶችን መመደቡ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ይሆናል። ምክንያቱም ሴቶች በህዝብ አስተዳደርና በመንግስት ገቢ አስተዳደር ከወንዶች ይልቅ የተሻሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ጥናታዊ መረጃ ባይ ርም ሀላፊነትን ከመሸከምና ህግን ከማክበር፣ ከእጅ መንሻ መቀበልና ከሙስና አኳያ ያለውን ልዩነት ጠቅለል ባለመልኩ ማየትና የህሊና ፍርድና መስጠት ይቻላል። ሌላው ደግሞ በየትኛውም ደረጃና እርከን ያሉት ሴቶች የገቢ ምንጫቸው የሚዳብርበትን ዘዴ ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የሴት ገቢ አደገ ማለት የቤተሰብ አመጋገብ፣ የልጆች በተሻለ መልኩ መማርና ጤንነት መጠበቅና በየተኛውም እረከን ላይ በውሳኔ ሰጪነት ሚና መጫወት እንድትችል እርምጃ መወሰዱን ያመለክታል።

የህዝብ ብዛታችን ማህበራዊ አገልግሎትን ለማዳረስ ካለው አቅማችን ጋር ስለማይጣጣም በገጠርና በከተማው ያለው ህብረተሰብ ወሊድ ቁጥጥርን እንደሚገባው አድርጎ ማስተማር በተለይም ወንዶች የበለጠ ሚና እነዲጫወቱ ማድረግ አስፈላጊነቱ ጥርጥር የለውም። የህብዝ ዕድገት ከልማት ጋር ሲመጣጠን በልማት ላይ የሚታየውን ክፍተት ለማጥበብ መንቀሳቀሻ በጀት እንዲ ርና ከጊዜ እጥረት የተነሳ በእቅድ ብቻ ተወስነን እንዳንቀር ይረዳል።

ስለሆነም የልማት መርሃ-ግብሮች እያንዳንዱን ክፍተት ለመሸፈን ከበጀት ጋር ዓላማ ይ መነሳትን ይፈልጋሉ። ይህ ካልሆነ ግን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ኤድስና ድርቅ ከድሮ በተለየ መልኩ በህዝባችን ላይ የመከራ፣ የሰቆቃና የዕልቂት አዋጅ እንደአወጀ ልብ ልንል ይገባል። ምክንያቱም የአገራችን ሴት ልጅ በባህል ተጽእ በበታችነት የምትተዳደር ከመሆኗ የተነሳ በአገር ውስጥ ለዝሙት አዳሪነት ተዳርጋ ባለትዳርም ከሆነች የባሏን ፍላጎት ብቻ አስተናግዳ በሰው አገር በስራ ስም ለዘመናዊ ባርነት በደላላ እየተሸጠች ባለችበት ኤድስ እንደሰደደ እሳት በቅጽበታዊ ፍጥነት እየገደለ ባለበት ዘመን የድህነት ጥያቄ የሴት ልጅ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የህዝቡ የልማት ጥያቄ ሊሆን ይገባል። ድህነት ጎልቶ የሚታየው የሴቶች መብት በሚረገጥባቸውና በጾታቸው መካከል የሰፋ ልዩነት ባለባቸው አገሮች ስለሆነ የሴቶች የመብት ጥያቄ የልማት ጥያቄ መሆኑን በማመን ሁሉም ዜጋ ሊታገልላት ይገባል።

**በአጠቃላይ፡-**

- ሴቶች ልዩ ልዩ ተቋማትን በባለቤትነት እንዲይዙ፣ እንዲያስተዳድሩና እንዲያንቀሳቅሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ፖሊሲዎችና መርሃ-ግብሮች በሴቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን በቅድሚያ እየገመገሙ መከላከል፣

- በትምህርት ላይ በሙሉ ኃይላቸውና በተረጋጋ መንፈስ እንዳያተኩሩ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን አስወግዶ በየደረጃው ማለትም ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ተቋም ድረስ በቁጥር ከወንዶች እኩል የሚሆኑበትንና በሳይንስና ቴክ ሎጂ የትምህርት መስክና ስልጠናዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- የወሊድ ቁጥጥር የቤተሰብ ጤንነትን ለመጠበቅም ሆነ የህዝብ ብዛትን ለመቆጣጠር ድርሻ ስለአለው በተለይም ወንዶች እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- የኤድስ መከላከያ ስልቶችን መቀየስና የእናቶችና የህጻናት ጤና እንክብካቤ ተቋማትን በጥራትና በብዛት ማዳረስ፣
- በተለያዩ ምክንያቶች የሚደርሱትን የሴቶችን መብት መጣስ ለማቆም የሚያስችሉ ህጎች ማጠናከር፣
- በስራ አመካኝተው ሴቶችን እያባበሉ ከገጠር ወደ ከተማ ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር የሚያስ በልሉትን መከታተል፣
- በስደትና በጦርነት ወቅት የሴቶችን መብት የሚጋፉ አካላት ጥብቅ ቅጣት እንዲቀበሉ ማድረግ፣
- በየትኛውም የሰላም ድርድር ወቅት የሴቶችን ተሳትፎ ማበረታታት፣
- የጦርነት ወጪዎችን ለመቀነስ ጥረት ማድረግ፣
- ሴቶች ወደ ስልጣን እርከን እንዲመጡ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም፣
- የመበደር አቅም  እንዲ ራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በጾታ የተተነተነ መረጃ ማሰባሰብና ማሰራጨት መቻል፣
- በሙያና በጾታ ማህበራት ማደራጀት፣
- ፖሊሲዎችና መረሃ-ግብሮች ከመጽደቃቸው በፊት የሴቷን ጥያቄ ማካተት አለማካተታችዉን መመርመርና ከበጀት  ጋር መታቀዳቸዉን ማረጋገጥ፣
- የሴቶችን በህግ የተደነገጉ መብቶች ሲጣሱ በቸልታ አለመመልከት፣
- የሰብዓዊ መብት ትምህርት በስፋት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- መገናኛ ብዙሀንን ሴቶች ማግኘትና መጠቀም የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የመገናኛ ብዙሀን ድርጅቶች በሁለንተናቸው ሚዛናዊ የሆነ አቀራረብ እንዲኖራቸው መርሀ-ግብር እንዲቀርፁ ማድረግ፣
- የሴቶችን የስራ ጫና ለመቀነስ የሚረዱና የአካባቢን እንክብካቤ የሚያጎለብቱ ዘመናዊ ሥልቶችን መጠቀም፣
- የወጣት ሴቶችን ሰቆቃ ለማስወገድ በስልጠና፣በክህሎት፣በትምህርት፣በውርስ ከወንድ እኩል የሚያሳትፉ ህጎችን ማውጣትና ተግባራዊነታችውንም መከታተል ቀጣዩ ትውልድ በልማት ላይ በእኩልነት እንዲሳተፍ ከማድረጉም በላይ ውጤቱ ሀገር እንድትለማ ያግዛል፡፡

## ዋቢ መፅሃፍት


Ethiopia: Sustainable Development and Poverty Reduction Programe MOFED 2002.

ኦክስፋም የሥርዓተ-ጾታ ሥልጠና መመሪያ ክፍል 3 ሥርዓተ ጾታና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች፡

Paper on Gender at the heart of Economic Planning. British council Sep. 2002

የጾታና ልማት መመሪያ ግብርና ሚ/ር ሴቶች ጉዳይ መምሪያ

The End of Welfare? Consequence of Federal Devolution for the Nation. Max V. Sawicky Armonk, New York London, England, 1999.

ብሄራዊ የሴቶች ጉዳየ ፖሊሲ መስከረም 1986

Women of Our World. Population Reference Bureau. Washington DC 2002

የሥርዓተ ፆታና ልማት ታሪካዊ አመጣጡ ይዘቱና የሚነሱ ጉዳዮች በዘውዴ አበጋዝ ግንቦት 1994

LDCs: Building Capacities for Mainstreaming Gender in Development Strategies, UNCTAD, UNDP, New York and Geneva 2002.

CERTWID INFORMS Vol. 6 No 1 September 2000

Gender, Growth and Poverty Reduction. Special Program of Assistance for Africa, 1998 Status Report on Poverty in Sub-Saharan Africa. The World Bank Washington D.C

# FSS PUBLICATIONS LIST

## FSS Newsletter

*Medrek* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

## FSS Discussion Papers

No. 1. *Water Resource Development in Ethiopia: Issues of Sustainability and Participation*. Dessalegn Rahmato. June 1999

No. 2. *The City of Addis Ababa: Policy Options for the Governance and Management of a City with Multiple Identity*. Meheret Ayenew. December 1999

No. 3. *Listening to the Poor: A Study Based on Selected Rural and Urban Sites in Ethiopia*. Aklilu Kidanu and Dessalegn Rahmato. May 2000

No. 4. *Small-Scale Irrigation and Household Food Security. A Case Study from Central Ethiopia*. Fuad Adem. February 2001

No. 5. *Land Redistribution and Female-Headed Households.* By Yigremew Adal. November 2001

No. 6. *Environmental Impact of Development Policies in Peripheral Areas: The Case of Metekel, Northwest Ethiopia*. Wolde-Selassie Abbute. Forthcoming, 2001

No. 7. *The Environmental Impact of Small-scale Irrigation: A Case Study*. Fuad Adem. Forthcoming, 2001

No. 8. *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. October 2002

No. 9. *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. December 2002

No.10. *Rural Lands in Ethiopia: Issues, Evidences and Policy Response.* Tesfaye Teklu. Forthcoming 2003

No.11. *Poverty and Household Food Security in Ethiopia.* Eshetu Bekele. Forthcoming 2003

## FSS Monograph Series

No. 1. *Survey of the Private Press in Ethiopia: 1991-1999*. Shimelis Bonsa. 2000

No. 2. *Environmental Change and State Policy in Ethiopia*: *Lessons from Past Experience*. Dessalegn Rahmato. 2001

## FSS Conference Proceedings

1. *Issues in Rural Development. Proceedings of the Inaugural Workshop of the Forum for Social Studies, 18 September 1998*. Edited by Zenebework Taddesse. 2000

2. *Development and Public Access to Information in Ethiopia*. Edited by Zenebework Tadesse. 2000

3. *Environment and Development in Ethiopia*. Edited by Zenebework Tadesse. 2001

4. *Food Security and Sustainable Livelihoods in Ethiopia*. Edited by Yared Amare. 2001

5. *Natural Resource Management in Ethiopia.* Edited by Alula Pankhurst. 2001

6. *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Special issue containing the papers of FSS' final conference on poverty held on 8 March 2002

## Consultation Papers on Poverty

No. 1. *The Social Dimensions of Poverty*. Papers by Minas Hiruy, Abebe Kebede, and Zenebework Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. June 2001

No. 2. *NGOs and Poverty Reduction*. Papers by Fassil W. Mariam, Abowork Haile, Berhanu Geleto, and Jemal Ahmed. Edited by Meheret Ayenew. July 2001

No. 3. *Civil Society Groups and Poverty Reduction*. Papers by Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. August 2001

No. 4. *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse. In Amharic. Edited by Meheret Ayenew. November 2001

No.5. *The Private Sector and Poverty Reduction [Amharic].* Papers by Teshome Kebede, Mullu Solomon and Hailemeskel Abebe. Edited by Meheret Ayenew, November 2001

No.6. *Government, Donors and Poverty Reduction.* Papers by H.E. Ato Mekonnen Manyazewal, William James Smith and Jeroen Verheul. Edited by Meheret Ayenew, February 2002.

No.7. *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Edited by Meheret Ayenew, 2002

## Books

◈ *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below*. Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2002

## Special Publications

*Thematic Briefings on Natural Resource Management, Enlarged Edition.* Edited by Alula Pankhurst. Produced jointly by the Forum for Social Studies and the University of Sussex. January 2001

## New Series

- **Gender Policy Dialogue Series**

No. 1 *Gender and Economic Policy.* Edited by Zenebework Tadesse. March 2003

- **Consultation Papers on Environment**

No. 1 *Environment and Environmental Change in Ethiopia*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. March 2003

- **FSS Studies on Poverty**

No. 1 *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers.* Papers by Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. March 2003.

## Forum for Social Studies

The Forum for Social Studies (FSS) is an independent, non-profit institution engaged in policy-oriented research on the development challenges facing Ethiopia. It provides an open forum for the discussion of public policy and promotes public awareness. FSS believes that encouraging broad participation in policy debates is an important contribution to the democratic process. To achieve its goals, FSS organizes public conferences, and publishes and distributes its research findings to policy makers and other government officials, civil society institutions, professionals, the business community, donor agencies and the public at large. This publication is meant to encourage public discussion of the issues concerned and their policy implications.

## Gender Policy Dialogue Series

These publications are based on papers presented and discussions held at FSS' Gender Policy Dialogue Series and are meant to stimulate debate and reflection on gender issues and policy initiatives.

## Address

Forum for Social Studies Tel. (251-1) 55 61 21/12 95 79/55 20
25
P.O.Box 25864 code 1000 E-mail:
fss@telecom.net.et
Addis Ababa, Ethiopia Web Site: www.
fssethiopia.org

## Financial support for the Gender Policy Dialogue Series and

**this publication was provided by the Department for International Development of the United Kingdom for which we are grateful.**

**We also wish to thank the Royal Netherlands Embassy for its generous financial assistance to FSS.**